የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
City Government of Addis Ababa
Ethics and Anti-corruption Commission

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTAA BULCHIINSA MAGAALAA FINFINNEE
CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA EDUCATION BUREAU

## የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ክበባት አደረጃጀትና የሚከናወኑ ተግባራት

# ለስነ-ምግባርና ጸረሙስና ክበብ አመራሮች የተዘጋጀ ስልጠና

# ይዘት

## ክፍክ አንድ

### የትምህርት ተቋማት ከስነ- ምግባር ግንባታ አንጻር ያላቸው ሚና

- መግቢያ
- ዓላማ
- ትምህርት
- የትምህርት ኣላማ
- ተማሪዎች እንዲሁም የትምህርት ማህበረሰቡ ሊያጎለብተው የሚገባ የስነ-ምግባር መርሆዎች

## ክፍል ሁለት

የት/ቤቶች የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ክበባት

የአሰራር ማኑዋል

የስነ-ምግባር ክበባት ምንነት

የስነምግባርና ጸረ ሙስና ክበባት ውጤታማ

ስራዎችን እንዲሰሩ ለማን ምን ይጠበቃል

# መግቢያ

የአ/አ/ስ/ጸረ ሙ/ኮ ካሉት ዓላማዎች አንዱ የትውልድ ሥነ-ምግባር እና የሞራል እሴቶችን መገንባት ነው

የሞራልና ስነ-ምግባር ግንባታ ዋንኛ ማዕከል ደግሞ የግልና የመንግስት ት/ቤቶች ናቸው

የሥነ-ምግባር ግንባታ ተግባር የሚጀምረውና ጽኑ መሠረቱ የሚጣለው ውስጥ ነው

ት/ቤቶች ላይ የስነምግባርና ጸረ-ሙስና ክበባትን በማቋቋም የስነምግባር ግንባታውን በልዩ ትኩረት መስራቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል

የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ክበባትን በማቋቋም በማደራጀትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ይህ ስልጠና ተዘጋጅቷል፡፡

# 2. የስልጠናው ዓላማ

**ዓላማ**

የትምህርት ማህበረሰቡ በትምህርት ተቋማት ላይ ሊጎለብቱ በሚገቡ የስነ-ምግባር ገዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ

በትምህርት ተቋማት ለሚቋቋሙ የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ክበባት ማንዋል ላይ የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ


# 3. ትምህርት

- ዜጎች በአስተሳሰብና ባህሪ የተሻለ ሀገር ተረካቢ ሆነው ከሚወጡባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ነው
- ትምህርት ዜጎች ተሰጥኦአቸውን የሚያገኙበት የተሰጥኦ መግለጫና ማጎልበቻ ማዕከል ነው
- ትምህርት ዜጎች የነገ ማንነታቸውን የሚያሳልጡበትና እራሳቸውን በእውቀት ፣ክህሎትና አመለካከት የሚያሳድጉበት ዘርፍ ነው
- የባህሪ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችሉ መልኩ እውቀት የሚገበዩበት የእውቀት መድረክ ነው



# 4.ትምህርት ቤት፣

- ዕውቀትን በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ለማስፋፋት የሚዋቀር ማዕከል ነው::
- የትምህርት ሥራዎችን ለማከናወን የሚረዱ የሰው ኃይል፣ የትምህርት ግብአቶችና የአሰራር ሥርዓቶችን የሚደራጁበት
- ዕውቀትን ለማስረጽ፣ ክሂሎት ለማጎልበትና ተሞክሮን ለማጋራት የተነደፉ የትምህርት ፖሊሲዎች፣ ሥርዓተ ትምህርቶችና ስትራቴጂዎች የሚተገበሩበት ነው::



- የትምህርት ተቋማት የራሳቸው እሴቶች አሏቸው::
- እሴቶቹና መርሆዎቹ ለትምህርት ፖሊሲና ስትራቴጂ የሚመነጩ ናቸው::
- እነሱም :-
  - *ለበማዳባት*
  - *ፍትሓዊነት*
  - *ሚዛናዊነት*
  - *ቅንነትና*
  - *ግልፅነት*



## የትምህርት ዓላማው ምንድን ነው ?

## ለምን ትማራላችሁ ?

# 4. የትምህርት ዓላማ



- የትምህርት ውጤቱ በተማሪዎች ላይ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ነው
- የትምህርት ዓላማው
  - በእውቀት
  - በክህሎትና
  - በስነ-ምግባር የጎለበት ትውልድ ማፍራት ነው


# 5. በተማሪዎች ሊጎለብቱ የሚገባ የስነ-ምግባር መርሆዎች

## 1. ቅንነት :-

- ቅንነት፣ በሥራም በምግባርም ኃላፊነትን ለመወጣት ወይም አደራን ለመቀበል ፍጹም ዝግጁ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

– ቅኖች፣

- ግልጽ ናቸው
- ሌሎችን ለማሳሳት፣ ለማታለል፣ ጥቅም ለማግኘት፣ ወዘተ፣ ብለው የሸፍጥ ሥራ አይሠሩም ፡፡
- አግባብነት ያለው፣ የተሟላ ነገር ግን ያልተጋነነ መረጃም ይሰጣሉ፡፡



# ለ. እውነትን መናገር

- ሰዎች ትክክለኛ ስብእናቸውን ተላበሱ የሚባለው እውነተኛ መሆን ከቻሉ ነው።
- እውነተኛ ሰው ለቆመለት ዓላማ ቅድሚያ በመስጠት ሥነ-ምግባር የተገነባ ነው።

ይህም ሲባል፤

- ነገሮችን በሐቅ ለማከናወን መሰዋእትነት የመክፈል ቁርጠኝነት አለው።
- ለታነጸበት ሥነ-ምግባር መርህ በመቆሙ ብቻ በውስጥ ደስታን ይጎናጸፋል።
- ተግባሩ ሁሉ በመርህ ላይ የተመሠረተ ነው።
- አቋመ ጽኑ ነው። «እውነትን ተናግሮ ከመሸበት ማደር» የሚለው ምሳሌ የሚሠራው ለአቋመ ጽኑዓን ነው።



# ሐ. ቃልን ማክበር

- ሰዎች የገቡትን ቃል ኪዳን በማክበር ቁርጠኛነታቸውን ማሳየት ይገባቸዋል፡፡
- በሥነ-ምግባር የታነጹ ተማሪዎች፣ መምህራንና፣የተማሪ ወላጆች የትምህርት አመራሮች ለገቡት ቃል ይታመናሉ፤
- ቃላቸው ተግባራቸውን የሚመረበት ሰንደቅ ነው፡፡




# ሠ. ታማኝነት

- መታመን፣ ለሥነምግባር መርሆዎች ተገዥ መሆን ማለት ነው፡፡
- በሥነ-ምግባር የታነጹ ተማሪዎች ፣ መምህራንና የትምህርት አመራር አካላትና ወላጆች ለሚወክሉት ት/ት ማህበረሰብ የታመኑ ናቸው፡፡
- በፍላጎት ግጭት ውስጥም አይገቡም፤
- ለጥቅም ሲሉ ሚስጢር አሳልፈው አይሰጡም



# ሠ. ከአድልኦ መራቅ/ፍትሐዊነት

- በሥነምግባር **የታነጸ ሰው በፍትሃዊነት** ጉዳይ **ቁርጠኛ** ነው፡፡
- የሰውን ልጆች ሁሉ **እኩል ያስተናግዳል**፡፡
- **ልዩነትን በመቀበል በመቻቻል መርሕ** ላይ ተመሥርቶ መሥራት ሌላው መገለጫው ነው፡፡
- ስህተቱን ለመቀበል ዝግጁና ፈቃደኛ ናቸው፤
- በአምክንዮና በመርህ ያምናሉ



# ፈ. ሕግን ማክበር

- መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው
  - ተማሪዎችና መምህራን ፣ ለሕግ ተገዥ ናቸው::
  - ከሥራቸው ጋር ተያያዥ የሆኑ ሕጎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን በሚያከብር መርህ ያመራሉ::



# ሸ. የባለደረቦችን ክብር መጠበቅ

- መልካም ስብእና ያላቸው ተማሪዎች፣መምህራን ፣የትምህርት አመራሮች የራሳቸውን፣ የሚሠሩበትን ተቋምና የባለደረቦችን ክብር መጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ ያውቃሉ፡፡

እሱም በሚከተሉት ሁኔታዎች ይገለጻል፤

- ❖ ኃላፊነትን በአግባቡ በመወጣት፤
- ❖ ስተቋሙ በሚመጥን ስብእና በመቅረብ (ንጽሕና፣ አለባበስ፣ ወዘተ፣) ፤
- ❖ የተቋሙን ገጽታ በመገንባት፤
- ❖ ምሥጢር በመጠበቅ
- ❖ የትምህርት አመራሮችና መምህራንና  መልካም ስብእና ያለው ዜጋ መቅረጽ ከቻሉ፣ እነዚህን ባሕርያት በእያንዳንዱ ዜጋ ማንነት ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡

# ቀ. ተጠያቂነት

- በሥነምግባር የተነጹ ተማሪዎች ፣የትምህርት አመራር አካላት ፣ ለሚወስኑት ውሳኔና ለሚያከናውኑት ተግባር ኃላፊነት ይወስዳሉ።
- ሌሎችም (ጓደኞቻቸው፣ ባልደረቦቻቸው፣ ተቋማቸው፣ ኅብረተሰቡ፣ ...) ለሚያከናወኑት ተግባር ኃላፊነት እንዲወስዱ ግፊት ያደርጋሉ፤ በጎ ተጽዕኖም ያሳድራሉ።



# ከላይ የተገለጹትን ተግባራዊ ለማድረግ ክበብ ማደራጀት ያስፈልጋል

# ክፍል ሁለት

## የት/ቤቶች የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ክበባት የአሰራር ማኑዋል

የካቲት 2016

# ዓላማ

የስነምግባር ግንባታውን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል የክበብ አደረጃጀት ተግባራዊ በማድረግ በመልካም ስነምግባር የታነፀ፤ ሀገርን የሚወድ፤ እና ሙስናን የሚጸየፍ ትውልድ ማፍራት ነው::

# የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ክበባት አስፈላጊነት

ለሞራል/ግብረገብ የሚሰጠው ትኩረት በመቀነሱ ተማሪዎች በከፍተኛ የሞራል/ግብረገብ እሴት እየተሸረሸረ በመምጣቱ የላቀ የስነምግባር ደረጃን ለማምጣት

እውቀታቸውን፤ ክህሎታቸውንና አመለካከታቸውን በማዳበር የመተግበር፤ የመቻቻል፤ የመግባባትና የመከባበር ባህልን እንዲያጎለብቱ ለማገዝ

# የስነ-ምግባር አበባት ምንነት

- የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና አበባት
  - የትምህርት ጥራትና ሥነ-ምግባርን ለማሻሻል በት/ቤቶች የሚመሠረቱ አበባት ናቸው
  - በትምህርት ክፍል ከትምህርት ጥራትና ከስነ-ምግባር መሻሻል ጋር ግንኙት ያላቸውን ችግሮች በመለየት የችግሩን መንስዔ በማንጠርና የስነምግባር ማሻሻያ ቴክኒክ በመጠቀም አዳዲስ መፍትሄዎችን ለማምጣት የሚያስችል አደረጃጀት ነው ፡፡

# የክበቡ አደረጃጀት

- የስነምግባርና ጸረ ሙስና ክበብ ተጠሪነቱ ለአስተባባሪ መምህርና ለክበቡ ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፡፡
- አስተባባሪ መምህሩ ደግሞ ተጠሪነቱ ለት/ቤቱ የተጓዳኝ ትምህርት አስተባባሪ ይሆናል፡፡
- የክበቡ ስራ አስፈጻሚ አባላት ከ5-7 ሲሆኑ
  - ሰብሳቢ፤
  - ምክትል ሰብሳቢ፤
  - ጸሐፊ፤
  - ገንዘብ ያዥ፤
  - የህዝብ ግንኙነትና
  - አባል ይኖሩቸዋል፡፡
- የክበቡ ስራ አስፈጻሚ የአገልግሎት የጊዜ ገደብ በየ 3 ዓመቱ ሌላ የክበብ ስራ አስፈጻሚ ይመረጣል

# የስነምግባርና ጸረ-ሙስና ክበባት ወርቃማ የሞራል ህጎች

- ታማኝነት

- ከአድሎ ነጻ

- አጠኔታ እና
- አክብሮት

# 2. የክበቡ ዋና ዋና ተግባር እና የልዩ ልዩ አካላት ሚና

## የክበቡን ዓላማ እውን ለማድረግ የክበቡ ዋና ዋና ተግባራት

1. መልካም ስነምግባር በመላበስና ዓርዓያ በመሆን በት/ቤት የክበቡን ዓላማ ማስተዋወቅና አባላትን ማብዛት፤
2. በት/ቤት ወይም በክፍል ውስጥ የሚታዩ የስነምግባር መጓደልን ለይቶ በማውጣት የሚሻሻሉበት ሁኔታ ላይ መምከርና
3. የት/ቤቱ የስነምግባር ክበብ አባሉች የመልካም ስነምግባር፤ የዕውቀትና የክህሎት የእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ መፍጠር፤
4. በስነ- ምግባር ክበብ ውስጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችንና ዕውቀቶችን ለሌላ ክበባትና ለት/ቤቶች ማዳረስ

# የቀጠለ...

5. ተማሪዎችን በማስተባበር ዓመታዊ ሀገር አቀፍ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ቀንን ማክበር
6. በት/ቤቱ የበጎ ስነ- ምግባር ጋናል ውይይት እንዲካሄድ ማድረግ፤
7. በሚኒ ሚዲያ የስነምግባር ማበልጸግ ግንዛቤ ማስጨበጫ ማካሄድ
8. በት/ቤትና በተቋማት የሙስና ወንጀል ከተከሰተ ለሚመለከተው አካል በመጠቆም መታገል
9. ክክበቡ አባላት ሞዴል የሆኑትን በመለየት የእውቀና ሽልማት የተሰጣቸው ተማሪዎችን በመጋበዝ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ፤

# የቀጠለ…

10. ከስነ-ምግባር ግንባታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የጥያቄና መልስ ውድድር ማድረግ

11. አባላት ማፍራትና ስብሰባ ማስተባበር የሚችል እንዲሁም አዳዲስ ሀሳብ ማፍለቅ የሚችልና ሁሉም በነፃነት ሀሳብን መግለጽ የሚችልበትን አካባቢ መፍጠር የሚችል መሆን ይገባዋል።

12. የክበቡን አባላት የስነምግባር ስውጥ እንዲያመጡ ለማስቻል እና የክበቡ አባላት አቋማቸውን አሚጠው በጥሩ ስነምግባር ትምህርታቸውን ጠንክረው እንዲከታተሉና ለሌሎች ተማሪዎች ምሳሌ እንዲሆኑ ለማበረታታት

# የስነምግባር ክበባት አስፈጻሚ ኃላፊነትና ተግባራት

- አባላት ምን አይነት የባህሪይ ለውጥ እንዲመጣ እንደሚፈልጉ መለየት፣
- የተለየውን የስነምግባር ችግር በምን መንገድ መፍታት እንደለባቸው መወሰን
- ከአባላቱ የተሻለ ሀሳብን ማግኘት፣ የተሻለውን ሀሳብ ለተግባራዊነቱ የሚያበረታታ ሁኔታ መፍጠር
- የክበቡን የአሰራር መኑዋል፤የስነምግባር ደንብ፤ የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የእለት ተዕለት ክትትል ያደርጋል፤
- የስነምግባር ግንባታ ስልጠና አዘጋጅቶ ይሰጣል፤
- የት/ቤቱን አመራሮችና የትምህርት ማህበረሰብ ከስነምግባርና ጸረ ሙስና ክበብ ምን እንደሚጠብቅ መለየት እና ከአባላቱ ጋር እንዴት እንደሚተገበር መወያየትና በስምምነቱ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፤

**የስነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ክበባት ውጤታማ ስራዎችን እንዲሰሩ ለማን ምን ይጠበቃል**

# ከት/ት ተቋማት የሚጠበቅ ሚና

- በትምህርት ቤት ውስጥ ግብረገባዊ እሴቶች እንዲጎለብቱ ተማሪዎች በግ-ብረገብ የሚታነጹበትን መድረክ ማመቻቸት፡፡
- የግብረገብ ባህርያት እንዲሰርጹ ሃላፊነት የተሰጣቸውን የስነምግባር ክበባትን ማገዝ፤
- የሥነምግባር ክበባት ከት/ቤቱ መምህራን፤ ሰራተኞችና ተማሪዎች ሲወገዱ የሚገቡ እኩይ ጠባዮችና ተግባሮችን ነቅሶ በመለየት እንዲወገዱ ጥረት ማድረግ፤
- መልካም ግብረገባዊ ድርጊቶችና ጠባዮች እንዲስፋፉና እንዲጎለብቱ ጥረት ማድረግ፡፡
- ክትትል ድጋፍ ግምገማና ግብረመልስ ማድረግና ይህም ትኩረት የሚያደርገው የክበቡ አደረጃጀትና አሰራር ፤ ከተማሪዎች የባህሪይ ለውጥ መምጣት፤ ከተማሪዎች ውጤት መሻሻል ጋር ማጣጣም

# ግብረገብን በማጎልበት የአስተዳደር ሰራተኞች ሚና

- በት/ቤቶች መልካም ስነምግባር እንዲጎለብት በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር ሰራተኞች በመልካም ሥነምግባራቸው ዓርአያ መሆን ፤
- የትምህርት ቤት አመራሮች መሆኖች የተናገሩትን ሆነው በመገኘት አርአያ ሆነው መገኘት ::
- በትምህርት ቤት ውስጥ መልካም ስነምግባርን ለማጎልበት የስነምግባር ግንባታ ስልጠና መስጠት፤ መልካም ሥነምግባር የሚያሳዩትን ማበረታታት፤
- በስነምግባራቸው የተመረጡ የቀደሙ የስራ ሃላፊዎች በተለየ ሁኔታ ሮል ሞዴል እንዲሆኑ ማድረግ፤
- የህብረተሰቡን ፍላጎት አክብሮ የመስራት ባህል በት/ቤቱ ውስጥ የዘወትር ልማድ እንዲሆን የአስተዳደር ሰራተኞች ሚናቸውን በመወጣት
- በት/ቤቱ ውስጥ ላሉ የስነምግባር እሴቶች መከበር እየኖሩ ማሳየት

# የመምህራን ሚና

- መምህራን በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን በእውቀት፣በክህሎት እና በአመለካከት (መልካም ስነምግባር) ለማጎልበት ቁልፍ ሚና መወጣት አላቸው
- መምህራን በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎቻቸው ከሚሰጡት እውቀት ባሻገር በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት እያንዳንዱ እንቅስቃሴ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸው የሥራ ባህል እንዲሁም ልማድ የተማሪዎቻቸውን የወደፊት ስብእና በመቅረጽ ረገድ የሚያሳድረው ተጽእኖ ከስርአተ ትምህርቱ ያልተናነሰ ነው፡
  - የመምህሩ የአለባበስ ስርአት፣
  - የጸጉር አቆራረጥ፣
  - የሰዓት አከባበር፣
  - የቋንቋ አጠቃቀም፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደራዊ ክንዋኔዎች....ላይ አርዓያ መሆን ወዘተ

# የክበቡ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

- በክበቡ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ፤
- በክበቡ ያልተሳተፉ አባላትን አባል እንዲሆኑ ማበረታታት፤
- የክበቡን እቅድና አፈጻጸም በጋራ መገምገም፤
- የእርስ በርስ የልምድ ልውውጥ በማድረግ የባህሪይ ለውጥ ማምጣትና ሙስናን መከላከል፤
- ባላቸው እውቀት ክህሎትና ጉልበት ለክበቡ ለኬታማነት አስተዋጽኦ ማድረግ፤

# የክበቡ አመራርና አባላት መብቶችና ግዴታዎች

## መብቶች፡

- አጀንዳ የማስያዝና  አስፈላጊ ሰነዶችን የማቅረብ፣
- ሃሳብን በነጻ የመግለጽ፣
- ድምጽ የመስጠት ወይም የልዩነት ሃሳብ የማስመዝገብ፣
- ክበቡ በሚወከልባቸው በተለያዩ የተሳትፎ አደረጃጀቶች ወይም  ጥሪዎች ላይ እንዲሳተፉ ወይም እንዲገኙ ሲወከሉ የመሳተፍና የመገኘት፣
- ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ለክበቡ አመራር በጽሑፍ አስቀድሞ በማሳወቅ በክበቡ ላይ ቋሚ ተወካይ የመሰየምና የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

## ግዴታዎች

- የስብሰባ ሰዓት ማክበር፣
- ቋሚ የስብሰባ ስርዓት መከተል፣
- በቂ ዝግጅት አድርጎ የመምጣትና በንቃት የመሳተፍ፣
- በስብሰባው ላይ እጅ በማውጣት ሲፈቀድ መናገር፤እንደዚሁም ሌላው እየተናገረ ንግግሩን ያለማቋረጥ፣
- በክበቡ አመራር የሚሰጠውን የግልና የቡድን ተልዕኮ የመወጣት፣
- የክበቡ አመራር እና የክበቡ አባላት ማናቸውም ውሳኔዎች ወይም አስተያየቶች በሚያስቀምጡት አቅጣጫ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ፤
- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሕጎችንና የለውጥ መሳሪያዎችን የማወቅ፣ ግንዛቤ የመጨመርና  ችሎታን ማሳደግ፣
- የክበቡ አመራሮችና አባላት በስራ አፈጻጸምም ሆነ በስነ-ምግባር አርአያ ሆኖ መገኘት እንዲሁም ዕቅድና ሪፖርት በተፈለገው ጊዜና በጥራት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፡፡

# የስነምግባር ክበባት አደረጃጀት

- የስነምግባር ክበባት ስብሰባ አባላት በጋራ ለአንድ አላማ እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር አባላት ሀሳብ ይሰዋወጣሉ፤ የትብብር መንፈስ ያዳብራሉ፡፡
- ስብሰባው በአግባብ ካልተመራ ተግባራቱ በአግባብ ሳይተገበሩ እና አባላቱም ሳይበረታቱ ይቾሳሉና ስብሰባው ውጤታማ እንዲሆን መጣር ይገባል፡፡ ስለዚህ **ስብሰባውን ውጤታማ እንዲሆን፡-**

1. መታቀድ አለበት
2. አባላቱ ስብሰባው ላይ መገኘት አለባቸው
3. ኃላፊነት መከፋፈል አለበት
4. የስብሰባው አላማ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ አለባቸው
5. አባላቱ በሙሉ ሀሳብ መስጠት አለባቸው
6. ቃለጉባኤ መያዝ አለበት

# የሥነ-ምግባርና ጸረ ሙስና ክበብ አደረጃጀት አፈፃፀም

1. የስነምግባርና ጸረ ሙስና ክበብ ለመመስረት ስምምነት ላይ መድረስ
2. የስነምግባር ክበብ አባላትን መመዝገብ
3. የክበቡን እቅድ ማቀድ
4. መተግበር
5. ማረጋገጥ
6. ምርጥ ተሞክሮን ማስፋት
7. ቀጣይ ክበብ አመራርና ፈጻሚ መለየት

አፍላጦን (Plato) እንዲህ አለ «መልካም ሰዎች በኃላፊነት ስሜት ለመሥራት ሕግ እስከሚነግራቸው አይጠብቁም፤ ክፉ ሰዎች ግን ከሕግ ማምለጫ መንገድ ይፈልጋሉ»